# ለተጠራ ኢትዮጵያን አድን ጥሪ ኢትዮጵያዊ ምላሽ

ኢትዮጵያችንን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ ሀገር ወዳድ ሀይሉ በተለያዩ የትግል ስልቶች ትንቅንቅ ላይ ይገኛል።

ነጻነት ያለ ህብረት እና ያለመስዋዕትነት እንደማይገኝ  ጠንቅቀን የምንገነዘብ ኢትዮጵያዊያን የጋራ ሥራውን በጋራ ግብረ ሀይል የአቅማችንን በማከናወን ላይ እንገኛለን፡፡

ኢትዮጵያንና ዜጎቿን በክብር፣ በፍትህ እና በእኩልነት ይኖሩ ዘንድ ለሚታገሉ ሀይሎች በሀሳብ፣ በቁስም ሆነ በማንኛውም መንገድ መተባበር የዜግነት ግዴታችን መሆኑን ስለምንረዳ በተጠራንበት ሀገር አድን  ጥሪ ሁሉ ለመሳተፍ የምንሳሳለት አንዳችም ነገር የለንም፡፡

በቅርቡም በሀገር ቤት ዝግጅቱን እያጠናቀቀ ያለውን የሕዝባዊ እምቢተኝነት ጥሪን ተቀብለን በመንቀሳቀስ ላይ እንገኛለን፡፡ ይህ ከሀገር ቤት የተላለፈውን የእንተባበር ጥሪ በዋሽንግተን ዲሲ እና አካባቢዋ የምንቀሳቀስ የጋራ ግብረ ሀይል ፤ አድማሳችንን በማስፋት በቅርብ እና በሩቅ ካሉ የኢትዮጵያ ነጻነት ናፋቂ ሀይሎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ሁለንተናዊ ድጋፍ ለማድረግ ተግተን እየሰራን ነው፡፡

ስለዚህ ይህንን የሀገር ቤት የትግል ነጋሪት ለሰማችሁ በግልም ሆነ  በስብስብ ለምትንቀሳቀሱ ሃይሎች ከዋሽንግተን ዲሲ የጋራ ግብረ ሀይል ጋር በመተባበር በህዝባዊ እምቢተኝነት ጥሪ ላይ አሻራችሁን እንድታሳርፉ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን፡፡

በጋራ ኢትዮጵያን እናድን!!!

ለበለጠ መረጃ እንዲሁም የግንኙነት መስመራችን፡-

dcjointtaskforce@gmail.com ወይም 703 408 0770 ,  571 403 2474 ,  202 607 3685

የዋሽንግተን ዲሲ የጋራ ግብረ ሀይል